በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ሳምንታዊ ስርጭት የስነጽሑፍ ክፍል የአገራችንን ሁኔታ እዬተከታተለ በሚያቀርበው የፖለቲካ፣የምጣኔ ሃብትና ማህበረሰብአዊ ጉዳዮች አምዱ በዛሬው እለት ከዬት ወዴት?በሚል እርእስ ላይ የሚከተለውን ትንታኔ አቅርቧል።እንብባችሁ ለሌላው ለማዳረስ ትብብራችሁን በአክብሮት እንጠይቃለን

# ከዬት ወዴት?

ሐምሌ 30 ቀን 2015 ዓም(06-08-2023)

በቅድሚያ ግን ሰሞኑን በአመስተርዳም ከተማ ተደርጎ በነበረው የኢትዮጵያውያን የእስፖርትና ባሕል ዝግጅት ላይ በመሳተፍ የዋንጫው ባለቤት ለመሆን የበቁትን የስዊድን ክለብ ተጫዋቾች እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እንወዳለን።ለማንኛውም አይነት የጋራ ድል ተባብሮ መሰለፍ ተገቢና ወሳኝ እንደሆነ፣በጠንካራ ቁመናና በተግባባ የጋራ ሥራ ለድል መብቃትም እንደሚቻል የምናይበት አንዱ መንገድ እስፖርት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ የገጠሙንን ችግሮችና ፈተናዎች ለማለፍ በጋራ መቆም እንዳለብን የሚጠቁመው አንዱ ምሳሌ በእስፖርቱ ሜዳ የሚገኘው ድልና ችንፈት ነው። ችሎታ፣ ስልትና ቅንብር ያለው አካል በተሰለፈበት ተግባር ለድል እንደሚበቃ እስፖርት አንዱ ማረጋገጫ ነው።

ምንም እንኳን ዝግጅቱ የተደረገበትን ጊዜ አገራችንና ሕዝባችን ካሉበት አንጻር በመነሳት ብዙ ተቃውሞ ቢኖርና እኛም የዚያ አካል ብንሆንም ዝግጅቱ በታዳሚዎቹና በተጫዋቾቹ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ መጠናቀቁ በመልካም ጎኑ እንዲታይ አድርጎታል።

ስለዝግጅቱ ብዙ የተባሉ ሲሆን በእኛና እኛን በመሰሉት በኩል የቀረበው ትችትና ተቃውሞ አገራችንና ሕዝባችን ባሉበት በዚህ የሞት የሽረት ወቅት እንዲህ አይነቱ ዝግጅት አላስፈላጊ እንደሆነ በማመን ሲሆን ዝግጅቱ በመንግሥት የተደገፈና በታወቁ የጥቅምና የዘረፋ ቡድኖች የተመራ መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች ከአገር ቤትና ከአመስተርዳም ዙሪያ በገሃድ የተገኙና የታዩ ማስረጃዎች ወጥተዋል። ከነዚያም መካከል ክንፉ አሰፋ የተባለ ልማደኛ ሌባ አገር ቤት ከገባ በኋላ የስርዓቱ ደጋፊ በመሆን የጅማ ወጣቶችን የእስፖርት እንቅስቃሴ እንዲመራ ሲመደብ፣ የአውሮፓውን የእስፖርትና የባሕል በዓል በመንግሥት ባጀት ተመድቦለት ከውጭ ካሉት ኢጋሮቹ ጋር በመተባበር ዝግጅቱን በግንባር ቀደምትነት መርቷል።የዚሁ ሌባ አንዱ ኢጋር መስፍን ታዲዎስ አማን የተባለ፣አክቲቪስት፣ፖለቲከኛና ዳቆን ነኝ በማለት የሚያምታታና የተምታታበት ግለሰብ ነው።ይህ ግለሰብ ባለፉት ጊዜያቶች የመኢአድ ፣የግንቦት ሰባት፣የባልደራስ አባል በመሆን የሥልጣንና የጥቅም በሮችን እያንኳኳ ሲገለባበጥ የኖረ ፣ ያሰበውን ሳያገኝና ለማዳከም ሴራ ሲጎነጉን ሲነቃበት ጥሎ የፈረጠጠ ወይም ተወግዞ የተባረረ ሰው ነው።ከአራት ዓመት ወዲህ ከክንፉ አሰፋ ጋር በመሆን የብልጽግናን በተለይም የአብይ አህመድን ስብእና በመገንባቱ እረገድ ስሚ የሌለው የሚድያ መስኮት ከፍተው እንደነበር ይታወቃል።ላበረከቱት ሥራም የገንዘብና የመሬት ዳረጎት እንዳገኙና መሬቱን እንደቸበቸቡ በውስጥ አዋቂዎች ይነገራል። ለሚጠይቃቸው የሚሰጡት መልስ ግን በውስጥ አርበኝነት የብልጽግናን ምስጢር ለማግኘትና ለተቃዋሚው ለማካፈል ነው የሚል ዓይናችሁን ጨፍኑና ላሙኛችሁ የሚል የተበላ ምክንያት ማቅረብ ነው።እነዚሁ ሃፍረተቢሶች አሁን መልክ እዬያዘና እዬተጠናከረ በመጣው የአማራው ትግል ውስጥ ሰርጎ ለመግባትም በማሽኮብኮብ ላይ ናቸው።አሁን የአማራው ትግል በመጠናከር የሥርዓቱን ሰፈር ሲነቀንቀው ካለምንም ይሉኝታ በመሰል የሚድያ መስኮቶች ብቅ እያሉ ከፋኖ በላይ ፋኖ ሆነው

መዘላበድ ጀምረዋል።በዚህም አይቆሙም ፤ሌላ ድርጅት ብቅ ካለም የሚንጠላጠሉበት ቀጭን ክር ለማግኘትና ሰርጎ ለመግባት የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። እንግዲህ የአመስተርዳሙ የእስፖርትና የባሕል ዝግጅት በነዚህና በመሰሎቻቸው የተመራ ነበር። በክንፉ አሰፋ የተመራው የአገር ቤቱ የእስፖርትና የሙዚቃ ቡድን አጅቦ የመጣው የባለሥልጣኖች ቡድን ተሸክሞት የመጣውን የፖለቲካ ተልእኮ ለማድረስ ሁኔታው ሳይፈቅድለት ቀርቷል። የነጋዴውና የፓርላማ አባሉ ዶር አሸብርና የሻለቃ ደራርቱ እንዲሁም የታዋቂው የፊፋ እግር ኳስ ዳኛ የሆነው የበአምላክ ተሰማ ካለመንግሥት እውቅናና ተልእኮ የተደረገ የግለሰቦቹ የመልካም ፈቃድ ጉዞ እንዳልሆነ የማይረዳ አለ ብለን አንገምትም። በተለይም ዶር አሸብርና ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ ለሥርዓቱ ያላቸው ቅርበትና በአብይ አምልኮ እንደተለከፉ የሚታወቅ ሃቅ ነው።ሁለቱም ግለሰቦች የአብይ አህመድ ደጋፊና አፈቀላጤዎች ከመሆናቸውም በላይ ለተረኛው የኦሮሙማ ቡድን በእስፖርት ሜዳና በፓርላማ መድረክ ላይ ሽፋን በመስጠት ይታወቃሉ።

ክንፉ አሰፋ ከ10 ዓመት በፊት በዚሁ አምስተርዳም ከተማ በተዘጋጀው ተመሳሳይ በዓል በገንዘብ ዘረፋ ተጠርጥሮ በኦዲተር የተረጋገጠበት ነበር።አብይ አህመድ ለኖቤል ሽልማት ኖርወይ ሲሄድም ሙሉ ዝግጅቱን በካሜራ የቀረጸው ይኸው ክንፉ አሰፋ ነበር።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው የእሱና የአብይ አህመድ የጅማ ልጅነታቸውን መነሻ በማድረግ ግንኙነታቸው የጠነከረው።ክንፉ አሰፋ እንኳንስ ከጅማ ጥቅም ካገኘ ከዬትም የመጣውን አገር አጥፊ ከመደገፍ አይመለስም።ይህ የክንፉ አሰፋ መታወቂያ ምግባሩ ነው።

ከአዲስ አበባ መጡ የተባሉት ተጫዋቾች አቅም ሲፈተሽ ለጉዞና በአመስተርዳም ውድ ሆቴሎች ለመሰንበቻ ወጭ ከፍሎ የሚመጣ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም።የሰፈር ኳስ ተጫዋች የደሃ ልጅ ይህንን ሁሉ ወጭ ከመንግሥት በኩል ድጎማ ካልተደረገለት ወይም በእስፖርቱ ስም ማልያ ለብሰው እንዲሮጡ የተደረጉ የባለሥልጣንና የጊዜው ባለሃብት ቤተሰቦች ካልሆኑ በቀር ይችለዋል ተብሎ አይገመትም። የደሃው ልጅ እንኳንስ አውሮፓ በሰፈሩም ውስጥ በነጻነት የመጫወት እድሉ የመነመነ ነው።በችግር የሚቆላ ወጣት አውሮፓ መጥቶ ኳስ ያንከባልላል ብሎ ማሰብ ያገሪቱን ሁኔታና የሕዝቡን ኑሮ አለመረዳት ይሆናል።የነዚህ ተጫዋቾች ቀጣዩ ጨዋታቸው በያገሩ ስደተኝነት ለመጠዬቅ የሚያቀርቡት የውሸት ትርክትና ድራማ ይሆናል።

ከአገር ቤት የመጡ ከ100 በላይ የሆኑ ሰዎች በተለይም ወጣቶች እስፖርት ክለብ ስምና በሙዚቃ እንዲሁም በንግድ ስም የወጡት ሜዳውን አጥለቅልቀውት እንደነበረ ታዝበናል።ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ከአገር ለመውጣት ለአዘጋጁ ቡድን ከፍተኛ ገንዘብ የከፈሉ ለመሆናቸው ውሎ ሳያድር የሚነፍሰው ወሬ ያረጋግጣል።የዚህ አይነቱ የንግድ ሥራ የተለመደ ነው፤ባለፉት ጨዋታዎችም ሰበብ ገንዘብ ከፍለው ፓስፖርትና ቪዛ ተሰጥቷቸው፣ማልያና የንግድ ሸቀጥ ታድለው ከጨዋታው ማግሥት ስደተኝነት የጠዬቁትን ስናይ የአሁኑም ዝግጅት የዚያው የሌቦች ኪስ የዳበረበት ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

ዝግጅቱን ከእስፖርቱ በላይ የመጠጥና የጭፈራው እንቅስቃሴ የሸፈነው ነበር።ወጣቱ ትውልድ አብዛኛው ከፖለቲካና ከአገር ጉዳይ ይበልጥ የሚስበውና የሚያረካው ጨዋታ፣ሙዚቃ፣ጭፈራና መጠጥና ሌላ ሌላውም መዝናኛ መንገድ ነው።በተለይም አብዛኛው በውጭ አገር የተወለደ ስለሆነ ስለኢትዮጵያ ያለው ግንዛቤ እንደወላጆቹ አይሆንም።ይህ ወጣት ትውልድ ሃላፊነት በሚሰማው፣በአገር ወዳዱ በአንጋፋው ትውልድ ካልተገራና ግንዛቤ እንዲኖረው ካልተደረገ ለባእዳን ባሕል፣ሴራና ለአገር አጥፊዎቹ በቀላሉ መሣሪያ ለመሆን የተጋለጠ ነው።በተለይም የኢትዮጵያ ቀን በሚለው ስያሜ ስለአገርና ሕዝብ ታሪክ፣አሁን ስላሉበት ሁኔታ፣ከወጣቱ ትውልድ ምን እንደሚጠበቅ መልእክቶች የሚተላለፉበት እለት መሆን ሲገባው በአስረሽ ምችው መርሃ ግብር መሸፈኑ ከእለቱ ስያሜ ጋር የሚቃረን ድርጊት ነው።

ሌላው ዝግጅቱን ከእስፖርት ይልቅ የንግድና የገንዘብ ግብአት እንቅስቃሴ የተከናወነበት አድርጎታል። ከሜዳ መግቢያው ከ10 ኤሮ ጀምሮ በዱምሽቱ የጭፈራ ቦታ ለመግቢያ ከሚከፈለው 50 ኤሮ ፣ እንዲሁም ለመጠጥ ከሚጠዬቀው ከፍተኛ ዋጋ፣ከመኪና ማቆሚያ ከሚጠይቀው የቀን ወጭ ጋር ተዳምሮ ታዳሚው ላልተጠበቀ ከፍተኛ ወጭ መዳረጉንና ብዙ ቅሬታም እንዳደረበት የተሰሙት ብሶቶች ያረጋግጣሉ።ከብሶቶቹ አንዱ በጠባብ የዘፈን አዳራሽ ውስጥ ከቁጥር በላይ የተጠቀጠቀው ህዝብ በምቾት አልባ ብቻም ሳይሆን ለከፈለበት ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የዘፈን አቅርቦት ሳያገኝ እንዲወጣ መገደዱ ነው።በዚህ መልክ የተሰበሰበው ገቢ ለዘራፊዎቹ እንጂ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ አላደረገውም። የእስፖርት ፌዴሬሽኑን የሚጠይቅም ሃላፊነት የሚሰማው ከለብም ሆነ ደጋፊ አለመኖሩ ለዘረፋው አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል።በአንዳንድ የስካር መንፈስ በተጫናቸውና ለበዓሉ የሚድያ ሽፋን በሚሰጠው የአብይ አህመድ ቅጥረኛ በሆነው በሆዳሙ ደረጀ ሃ/ወልድ በኩል ስለዝግጅቱ ስኬትና መልካምነት የተገለጸ ቢሆንም ጠለቅ ብለው ካዩት ግን ብዙ አጨቃጫቂና ጉድለት የተሞላበት ዝግጅት መሆኑ በመገለጽ ላይ ሲሆን ይበልጥ እያደር ወደ ገንዘብ ክፍልፍሉ ሲገባ ጎልቶ የሚወጣ ይሆናል። ወትሮም ሌባ ሲሰርቅ እንጂ ሲካፈል መጣላቱ አይቀሬ ነው።

በሜዳው ዙሪያ በተተከሉ ድንኳኖች የተለያዩ ድርጅቶች በምግብ ሽያጭና እርዳታ በመጠዬቅ ካዝናቸውን አዳብረውበታል።የቤተክርስቲያን፣የእርዳታ ተቋማት--- ወዘተ የማይናቅ ገቢ ማግኘታቸውን ከተጠቃሚው ሰልፍና ወረፋ ለመረዳት ይቻላል።እንደ ባሕል ሆኖ ግን የተገኘው ገቢ ለሕዝቡ ይፋ ሲደረግ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።በተለይም በቤተክርስቲያን ዙሪያ የሚደረገው አስተዋጽኦ የታቦት ሙዳይ አይመረመርም፣ሰጠሁም አይባልም በሚለው ሽፋን ተድበስብሶ ምስጢረ ሥላሴ በመሆን የቀሳውስቱና በዚያ ዙሪያ ያሉ ተጠቃሚዎች ግብአት ሆኖ መቅረቱ የተለመደ ነው።ምእመናኑ የመጠዬቅና የማወቅ መብታቸውን በግዝትና ቅስፈት ፍርሃት እንዳያስከብሩ መሆናቸው የተለመደ ሆኗል።አንዱ የሙብት ትግል በዚህም ዙሪያ የሚፈጸመውን ዘረፋ ማውገዝና ማጋለጥ ስለሆነ በዝምታ ላለማለፍ ህሊናችን ያስገድደናል።ሌላውም መብቱን ተጠቅሞ መጠቀሚያ ላለመሆን መነሳትና መጠዬቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።በእርዳታ ስምም የሚሰበስቡትን እንዲሁ።

የሚቀጥለው ጨዋታ በኢትዮጵያ ሊሆን እንደሚችል ጭምጭምታ ሰምተናል።ይህ እቅድ የሰነበተ ቢሆንም በኮሮና ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል።ለወደፊቱ ግን ላለመሆኑ ማስተማመኛ የለም።ከአዲስ አበባም ቡድን ማምጣቱ ያንኑ ለማመቻቸት ነው።እንደማገኛውም ተጋጣሚ የማዘጋጀት ዕድሉ ይሰጠውና እቅዱ ይሳካል ማለት ነው።የዬክለቦቹን አመራሮች በጥቅም በመደለል ድምጽ እንዲሰጡና እንዲደግፉ ለማድረግ የተቀመረ አሻጥር መኖሩን ከነክንፉ አሰፋ ከመንግሥት ጋር ካላቸው ቀረቤታ፣ ከአሁኑ አካሄዳቸውና ካልሰከነው የሌብነት ተግባራቸው ጋር አያይዞ ማዬት ይቻላል።በሥልጣን ላይ ያለው የኦነግ ቡድን ከቆዬና በአገር ቤት ውስጥ ከተደረገ ሌላው መልእክት የውጩ ዲያስፖራ ለመንግሥት እውቅና እንዳለው ከሚያሳዬትም በላይ የሕዝቡን የትግል ስሜት የሚበርዝና የወጣቱንም ስሜት በሌላ መንፈስ የሚበክል ይሆናል። ይህ ከመሆኑ በፊት በአውሮፓ የሚገኙ የፌዴሬሽኑ አባል ክለቦችና ደጋፊዎች ሊያስቡበት ይገባል።የእስፖርት ፌዴሬሽኑ ባለቤት ማህበረሰቡ ስለሆነቱ ከሌቦቹ እጅ ማላቀቅ ይኖርበታል። የተመረጠ አመራርና ኦዲተር ያለው ተቋም ሆኖ ፣የአሁኑ ዝግጅት ገቢና ወጭ በዝርዝር እንዲቀርብና በተመረጡ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ማድረግ አለበት።

የእስፖርቱን ጉዳይ ለጊዜው እዚህ ላይ አቁመን ወደ ሌላው ስናልፍ

ቤተ እምነቶቻችም ቢሆኑ እንደ እስፖርትና ሌሎቹ ማህበረሰብአዊ ተቋማትና እንቅስቃሴዎች በጎሰኛው ስርዓት ህሳቤና መንፈስ የተበከሉ ሆነዋል።አገር ለማፍረስ ታጥቆ የተነሳው የኦነግና ወያኔ ጥምር ቡድን በኦርቶዶክስ ተዋህዶና በሙስሊሙ ላይ የመዘዙት ሰይፍ ወደ አፎቱ አልተመለሰም።እስከአሁንም ድረስ

መፍትሔ ያላገኘ የተባባሰ ችግር ሆኗል።በተላላኪ ሰርጎ ገቦች በኩል የአነግን ፓትሪያርክና ጳጳሳት የመሾም ሂደትን ተከትሎ የወያኔ ፓትሪያርክ ሹመት በአክሱም ተካሂዶ ጭቅጭቁንና ቀውሱን አጡዞታል ብቻም ሳይሆን አገር የማዋለዱን ሴራና ሂደት ከግማሽ በላይ መንገድ ወስዶታል።የቀረው ግማሽ መንገድ አገር ወዳዱን በተለይም የአማራውን ማህበረሰብ በጉልበት ማንበርከክና የወልቃይትንና የራያን ለም መሬቶቹንና መውጫ በሮችን መቆጣጠር ነው።ይህ ግን በቀላሉ የሚሳካ አይሆንም። የአማራው ተወላጅ ከመቸውም ጊዜ በተሻለ ደረጃ ተደራጅቶና ታጥቆ እምቢ ላገሬ፣እምቢ ለሙብቴ ብሎ በጫካና በከተማ እዬተፋለመ ይገኛል።ይህንን ሃይል ለማዳከም ብሎም ለማፍረስ መከላከያ የተባለው የአነግ ጦር ብቻም ሳይሆን በሆዳቸው የተገዙ የራሱ ተወላጆችን በማዝመት ያልተሳካ ጦርነት ከተከፈተ ሰንብቷል።አሁን ይባስ ብሎም የክልሉ መሪ ነኝ የሚለው ይልቃል ከፍአለ(ዝቅአለ ቢባል ይመጥነዋል) የተባለው ወራዳ የአብይ አህመድ ባርያ በገዛ ሕዝቡ ላይ የመከላከያ ሃይል ገብቶ እንዲጨፈጭፍ በደብዳቤ ጠይቋል።ይህ ለአነግና ለወያኔ ጭፍጨፋ ፈቃድ የሚሰጥና ላለመጠዬቅም ሕጋዊ ምክንያት ይሆናል።በተጨማሪም የአማራው ሕዝብ በሁሉም አቅጣጫ በጦር ሲማገድ አነግና ወያኔ የሚፈልጉትን መሬት ነጥቀው ለመውሰድ ያመቸናል ብለው ያቀዱት ወረራ ነው።ሆኖም ግን ምንም መራርና አዳጋች ቢሆን ድሉ የአማራው እንደሚሆን ከአሁኑ የሚታዩት ውጤቶች ያረጋግጣሉ። የፋኖ ሕዝባዊ ሃይል በኮከብ ፍጥነት ከባቢዎችን ነጻ ኢያወጣ በመቆጣጠር ላይ ሲሆን ወደመጨረሻው ግቡ እዬገሰገሰ ነው።ይህንን የተመለከቱ የሌላው ማህበረሰብ ተወላጆች በተለይም የሲዳማ፣የጉራጌ፣ የወላይታ፣የከንባታ በአጠቃላይ የደቡብ ክልል ኢትዮጵያውያን ከአማራው ጎን እንደሚሰለፉ በይፋ ገልጸዋል።የነዚሁ ማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑ የመከላከያ አባላቱም ከብርሃኑ ጁላ እዝ በመውጣት መሣሪያቸውን ይዘው በመኮብለል፣እጃቸውን በመስጠትና በመቀላቀል አጋርነታቸውን አሳይተዋል። የወያኔና የአነግ ጸሃይ ደመና የጋረዳት ብቻም ሳይሆን በመጥለቅ ላይ ነች።ብልህ ሳይመሽበት ትግሉን ይቀላቀላል፤ሆዱ የበለጠበት ደግሞ በጥይት ይቆላል።

ከአማራው ውጭ ሌላው ማህበረሰብ ደልቶትና በሥርዓቱ እረክቶ ይኖራል ማለት አይደለም።ሁሉም በዬቤቱ የመከራና የስቃይ ኑሮ እዬገፋ ነው።ሌላው ቀርቶ በርሃብ አለንጋ የሚገረፉ የኦሮሞና የትግራይ ተወላጆች መኖራቸውን መካድ አይገባም።ችግራቸው በወያኔና በአነግ ኦርኬስተራ ተከልሎ እንዳይደመጥ ሆነና ደልቷቸው የሚኖሩ ደጋፊ አስመስሏቸዋል።የወያኔን ጵጵስና ሹመት የተቃወሙ የትግራይ መነኮሳትም እንዳሉ ይሰማል። ይህንኑ ሕገወጥ የፓትሪያርክና የጳጳሶች ሹመት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሕጋዊ ሲኖዶስ የተቃወመው ሲሆን አማጽያኑ ከቤተክህነት አላፊነት ቦታና ሹመት ተነስተው፣ እንዲሁም የነበራቸው ማዕረግ እንደተገፈፉ መግለጫ አውጥቷል።አያይዞም የይቅርታ ደብዳቤ ጽፈው ለመመለስ እንደሚችሉ የገለጸ ሲሆን ይህ ለዳግመኛ ስህተት በር የሚከፍትና ከነሳውሪዎስ አለመማር ማለት ነው። ክርስቲያኑ የትግራይ ተወላጅ ማወቅ ያለበት ወያኔም ሆነ በወያኔ ዙሪያ የሚፈጠሩ እንቅስቃሴዎች ለሙብቱና ለነጻነቱ ብሎም ለእድገቱ የሚያበቁት ሳይሆን በጠባብ መሬት ላይ ለአቦይ ስብሃት፣ለደብረጽዮን፣ለታደሰ ወረደ፣ለጻድቃን፣ለጌታቸው እረዳና ለመሳሰሉት ሥልጣንና ጥቅም የሚደረግ የማሳሳት እርምጃዎች ናቸው።በአዲስ አበባና በውጭ አገር ያካበቱትን ሃብት ሳይሆን በመቀሌ የገነቡትን የመኖሪያ ሠፈሮቹን ልዩነት ማዬቱ ይበቃል።ገና ከጅምሩ ኦርቶዶክስን አከርካሪውን እንሰብረዋለን ያሉትን ልብ ማለት ይበቃል።የአሁኑ የፓትሪያርክ ሹመትና ማፈንገጥ የዚያው አካል ነው።

በሽዎች የሚቆጠሩት የትግራይ ወጣቶች ሞትና መቁሰል እነዚህን እፉኝቶች ለዳግማዊ ሥልጣን አበቃ እንጂ ሕዝቡ የተነገረውን የተስፋ ዳቦ አልገመጠም።የትግራይም ሆነ የሌላው ማህበረሰብ ተወላጆች እንደ አማራው ፋኖ ለብሶታቸው የሚቆም ጀግና አለመፍጠራቸው ግን ከወንጀለኛው ቡድን ጋር እንዲታዩ አድርጓቸዋል።እንደ አማራው በቃን ብለው ላለመነሳት ከስርዓቱ ጋር በጎሳ እትብት የተሳሰሩ

ብዙዎች ናቸው።የአማራው ትግል መልክ ከያዘና ከጠነከረ ግን ከሱ ጋር የሚሰለፉበት ዕድል ከፍተኛ ነው።ለዚያም በትግሉ ውስጥ የሚሳተፉበት ዕድል መኖር አለበት።አማራ አንገልም ብለው ከመከላከያ የሚኮበልሉት የሌላው ጎሳ ተወላጆች የእንቅስቃሴው አካል ሊሆኑ ይገባል።ምክንያቱም አማራው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ነጻነትና አንድነት ስለሚታገልና በታሪኩም ያስመሰከረው ይህንኑ በመሆኑ ነው።

በእስፖርቱም ሆነ በእምነት ተቋማት ዙሪያ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን መልካምና ጎጂ ድክመቶችን፣ በአገርና በወገን ስም የሚፈጸሙትን ውንብድናና ወንጀሎች በማዬት የዛሬውን የስነ ጽሁፍ ክፍላችንን ጥንቅር ከዚህ ወዴት ? እንዴትስ በሚለው እርዕስ ስር የሚከተሉትን በማቅረብ እንደመድማለን።

አገር አፍራሹ የወያኔና የኦነግ ጥምር ሃይል በአገር ወዳዱ ማህበረሰብ በተለይም በአማራው ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት እያጠናከረው እንጂ እዬቀነሰው አልመጣም።ሁሉም ጸረ-ሕዝብ ስርዓት የመውደቂያ ጊዜው ሲቃረብ እብድ ውሻ ይሆናል፤ሁሉንም ይነክሳል፣ይለከፋል።ብልጽግናም ይህንኑ እኩይ ተግባር በመፈጸም ላይ ተሰማርቷል።በአዲስ አበባ ከተማ ወጣቱን እያፈሰ በእስርቤት በማጎር ብቻም ሳይወሰን የሥርዓቱ አካል በመሆን በፓርላማውና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተመርጠው የተመደቡት የአብኑ ክርስቲያን ታደለና የብልጽግናው ዶር ካሳ ተሻገር በሚያሰሙት ተቃውሞና በሚያቀርቡት ጥያቄ ምክንያት በሕግ ሊከበርላቸው የሚገባው መብታቸውን ተገፈው እንደ ተራ ወንበዴ በውድቅት በቤተሰቦቻቸው ፊት እዬተደበደቡ ወዳልታወቀ ቦታ ተወስደዋል።

ሥርዓቱ ለሚፈጽመው ወንጀል መሣሪያ የሚያደርገው ደግሞ ለሆዱ ያደረውን ደካማ ነው። በዚህ ደካማ አድርባይ ላይ ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ለትግሉ እንቅፋት የሆነውን እንደማሶገድ ስለሚቆጠር በምክር አልመለስ ያለውን መቅጣት ተገቢ ነው።ከሁሉም በፊት በራስ ውስጥ የጽዳት ዘመቻ መከናወን አለበት።ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው አስቀድሞ መምታት አሾክሿኪውን ነው። ተብሎ የለ!

ሌላው በሆድአደር ምሑራኖች በኩል የተሳሳተ ትንታኔ በማቅረብ የተቃውሞ ጎራውን በሃሳብ ልዩነት ሽርሽሮ ለማዳከም የሚደረገው ጥረት ነው።ይህም በተገቢው መንገድ ወጣቱን በማስተማር የነሱ ሰለባ እንዳይሆን ማድረግ ከእውነተኛ አገር ወዳድ ምሑራን ይጠበቃል።በተለይም በምዕራባውያን የሚዘወረውን ለዘረፋና ለብዝበዛ አመች የሆነውን ፣አገራትን ለመበታተን የታቀደ የወያኔና የኦነግ ጎሳ ተኮር ፍልስፍና የማጋለጡ ተግባር ሊጠናከር ይገባዋል።የውጭና የውስጥ ጠላቶችን መለዬት ለትግሉ ውጤት ወሳኝ ነው።

የአንድ አገር ነጻነትና ህልውና የሚጠበቀው በትውልዱ ቆራጥና አገር ወዳድ መንፈስ መኖር ነው።ይህ ደግሞ የሚቻለው ወጣቱ ትውልድ ያገሩን ታሪክና ባሕል ከዘመናዊ እውቀትና አስተሳሰብ ጋር አጣምሮ ሲገኝ ነው።በአጉል የውጭ አገር ባሕል፣ልማዶችና ፍላጎቶች የተበከለ ትውልድ እንኳንስ ለአገሩ ለራሱም አይበጅም፤መጨረሻውም አያምርም። ስለሆነም በዬከተማው እያውደለደለ ጊዜውን ፣ጉልበቱን፣ገንዘቡን በአጉል ቦታና ልማድ ላይ የሚያፈሰውን ወጣት ከአድራጎቱ እንዲርቅ መምከርና መመለስ አለያም ተገቢ የእርማት እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል።ስለሆነም አሁን የሚታዬው በቁማር፣ በጫት፣በአልኮል፤በእጽና በዝሙት ተግባር ላይ የተሰማራውን ወጣት በገንቢ ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ የትግሉ አንዱ አካል ሊሆን ይገባዋል።ይህንን የጥፋት መንገድ የሚያዘጋጁትንና የሚከፍቱትን እራስ ወዳዶች ገንዘባቸውን በሌላ ጠቃሚ ዘርፍ እንዲያውሉ መምከርና መመለስ ካልተቻለም መቆጣጠር ያስፈልጋል።

በምዕራቡ ዓለም የተከፈተው ከባሕልና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ የሆነውን የግብረሰዶማዊ ዘመቻ መታገል አገርን ማዳን ብቻም ሳይሆን ትውልድን ብሎም የሰው ልጅ ዘርን የማዳን ግዴታ ነው።ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ በመንግሥት ይውንታ በመስፋፋት ላይ ያለውን ይህንን ሰዶማዊ እንቅስቃሴ እንዳይስፋፋ ማድረግ ብቻም ሳይሆን ከበቀለበት ቦታ መመንጠር፣ይህንን እርኩስ ተግባር የሚያራምዱትን መቅጣት፣ የውጭ አገር ተቋም ወይም ዜጋ ከሆነም ከአገር ማባረር ወደመጣበት መመለስ፣የሚተገበሩበትን ቦታዎች፣ሆቴሎችና ክለቦች መዝጋት አስፈላጊ ነው።ለዘመቻው መሳካት የትውልዱና የእምነት ተቋማት መሳተፍ ግዴታ ነው።

ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ሰላምና ለሕዝቧ እኩልነት ብሎም ለእድገትና  መልካም ኑሮ የሚያበቃውን ጸረ ወያኔ/ኦነግ ትግል መሳተፍና መርዳት የሁሉም አገር ወዳድ ብቻም ሳይሆን ለሰብአዊ መብትና ለዴሞክራሲ ከቆመ ሁሉ የሚጠበቅ ነው።ይህንንም ተሳትፎ በልዩልዩ መንገድ መግለጽ ይቻላል።

ሕዝባዊው እንቅስቃሴ አገራችን ከገባችበት ማጥ የሚያወጣና ለዘለቄታው አንድነቷንና ነጻነቷን በሚያስከብር፣ ለብሔራዊ እድገት በሚያበቃ፣ ሕዝቧንም ካለበት የሰቆቃና የድህነት፣የጭንቀትና የመከራ ኑሮ የሚገላግል፣ የፖለቲካና የምጣኔ ሃብት መዳረሻውን በግልጽ ያስቀመጠ ፍኖተ ካርታ ሊኖረው ይገባል።ትግሉ ከብሶትና ከእልህ የተላቀቀ ለስርነቀል ለውጥ የሚያበቃ ፋና ወጊ ሊሆን ይገባል።ለጊዜያዊ ድልና ለግለሰቦች የሥልጣን መወጣጫ  መሆን የለበትም።ያ ካልሆነ ለውጥ ሳይመጣ ውሃ ቅዳ ቅሃ መልስ ከመሆን አይድንም። ለአሁኑ አገር አድን ትግል ትግሉን የሚመራ ከሁሉም የተውጣጣ ማእከል አስፈላጊ ነው።በቀጣይም የሽግግር ስርዓት እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች በተጓዳኝ ሊሠሩ ይገባል።

1 አቅሙ የፈቀደለትና የመዋጋት ፍላጎት ያለው የፋኖን ጦር በመቀላቀል፣

2 የፖለቲካ ንቃትና እውቀት ያለው ሌላውን በማስተማርና በመቀስቀስ የታጋዩን አድማስ በማስፋት ተግባር ላይ መሰማራት፤የምስጢር ሴሎችን በማቋቋም መረጃ መቀባበል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

3 አገር ወዳዱ ባለሃብት ለትግሉ አስፈላጊ የሆነውን የስንቅና ትጥቅ(ሎጂስቲክስ)አቅርቦትን በማሟላት ኢጋርነቱን ማሳዬት፤

4 የሕክምናና የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤት የሆነው ዜጋ በሙያው ለሕዝባዊ ጦሩ የነጻ አገልግሎት እንዲያቀርብ ሁኔታውን ማመቻቸት፤

5 ከአገዛዙ ነጻ በወጡ አካባቢዎች ሕዝባዊ አስተዳደርና መዋቅር ለመዘርጋት የሚያስችለውን ምክርና ድጋፍ እንዲሁም ግብአት ማቅረብና መሟላት የሁሉም ግዴታ ነው።የመንግሥት ንብረት፣የባንክ፣ የመከላከያ፣የፖሊስ፣የእስርቤቶች፣የፍርድቤቶች ---ወዘተ ሰነዶችና መዝገቦች እንዳይዘረፉ ወይም እንዳይወድሙ ጥንቃቄ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል።በተለይም በዘረፋና በውድመት ላይ፣እንዲሁም ለጠላት መረጃ በማቀበል  በተሰማራ ወንበዴ ላይ ከፍተኛ አይቀጡ ቅጣት መጣል ተገቢ ነው።

6 በኑሮ የሚጠበሰው ፣በሥራ አጥነት የሚሰቃዬው በተለይም የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ለስርዓቱ ላለመገዛት የእምቢተኝነት አቋሙን እንዲገልጽ  የነቃው ወገን በሚስጥር ማደራጀትና መምራት ይጠበቅበታል።

7 ለቁጥር የሚያታክቱ ለሥርዓቱ ታማኝና አገልጋይ የሆኑና እውቅና የሰጡ የፖለቲካ ድርጅቶች ባሳለፉት የአድርባይነት ተግባር ተጸጽተው ሕዝቡን ይቅርታ በመጠዬቅ በተግባራቸው ላለመቀጠል ወስነው ድርጅታቸውን አፍርሰው በአንድ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመካተት ፈቃደኛ በመሆን

በተግባር የተጀመረውን አገር አድን ሕዝባዊ የፋኖ ትግል በመደገፍ ግልጽ አቋም መያዝ አለባቸው እንላለን።የፓርቲ ችግር ያለ ይመስል በዬጊዜውና በዬመንደሩ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋሙ ሊወገዝ ይገባል።ይህ የመከፋፈሉን ወርድና ስፋት የሚያሳድገው ተጨማሪ እራስ ምታት እንጂ የዴሞክራሲ መብት ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም።ይሁን ከተባለ 120 ሚሊዮኑ ሕዝብ የዬግሉ ፓርቲ እንዲኖረው ከመፍቀድ ተለይቶ አይታይም።የፓርቲዎችና የክልሎች መብዛት የችግሮቻችን ምንጮች ናቸው። የአገራችንን የህብረተሰብ አሰላለፍ በሚወክሉ፣የዘመኑን ፖለቲካ በሚያንጸባርቁ አገር ወዳድ በሆኑ ከሦስት የፖለቲካ ፓርቲዎች በላይ አስፈላጊ አይደሉም። የሚመሩበት ፍልስፍና ያላቸው የግራ፣የቀኝና የመሃል ሰፋሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቂ ናቸው።በጎሳ የተደራጁት ፓርቲዎች የግል ጥቅማቸውን ወደጎን ትተው እንወክለዋለን የሚሉትን ማህበረሰብ ለአገር አድኑ ትግል አካል እንዲሆን ማዘጋጀትና ማሰለፍ ይጠበቅባቸዋል።ለወደፊቱ ግን በጎሳና በሃይማኖት መደራጀት በሕግ መከልከል ይኖርበታል።

በሰሞኑ የተሰማው በአቶ ልደቱ አያሌው ተቋቋመ የተባለው የፖለቲካ ፓርቲ አስፈላጊነቱ አይታዬንም፣ በውጭ አገር ለዚያውም በአሜሪካ ተመስርቶ እንደሸቀጥ አገር ቤት የሚገባ የፖለቲካ ፓርቲ ተቀባይነቱ እስከዚህም ነው።በሕዝብ መሃልና ፍላጎት እንዲሁም ተሳታፊነት ያልተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ከሚሰጠው ጥቅም ይበልጥ ጉዳቱ ያመዝናል።ለአቶ ልደቱ የሚሻለውም ያለፈ ስሙን በሚያድስበት መንገድ ለሕዝባዊ ትግሉ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

8 የውጭ አገራትን በመተማመን የሚደረግ ትግል የጌታ ለውጥ ፍለጋ ከመሆን ያለፈ ባለመሆኑ ከውጭ ተጽእኖና ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነ ሕዝባዊ ትግል ማድረግ የሚያዋጣና ዘላቂነት አለው።ስለሆነም በራስ መተማመን በሚለው መርሆ መመራት ለዘላቂ ነጻነት ዋስትና ስለሆነ የምዕራቡንም ሆነ የምስራቁን ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው አጎብድዶ እሩጫ ሊቆም ይገባዋል።ምዕራባውያን ለጥቅማቸው እንጂ ለሰማይ ቤት የሚሠሩ መነኮሳት አይደሉም።በአገራችን የሰፈነው ስርዓት የነሱ የቤት ሥራ ውጤት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።ትግላችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከነሱ ጋር ነው።

ከአገራት ጋር የሚኖረው ግንኙነት በጋራ ጥቅምና መከባበር ላይ እንጂ በጌታና በባሪያ መካከል ባለ በላኪና በተላላኪ መካከል የሚኖር ግንኙነት መሆን አይገባውም።

በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ ከላይ በተጠቀሱት የትግል መስኮች ለመሳተፍ ይችል ዘንድ አንድ ማእከል መፍጠር ያስፈልገዋል።የአገርቤቱም ትግል እንዲሁ አንድ የትግል ማእከል ሊኖረው ይገባል። በተዝረከረከና በተበታተነ መልኩ የሚካሄድ ትግል ለጠላት አመች ይሆናል፤ለድልም አያበቃም። የውስጡና የውጩ የሚገናኙበት ሰንሰለት ሊፈጠር ይገባል።አሁን እንደሚታዬው ከሆነ ግን ለመቆጣጠር በማይቻል መልኩ ሁሉም በዬፊናው የፈለገውን የሚያደርግበት አሠራር ነው። ስብሰባውም፣እርዳታውም፣ቅስቀሳውም በተጻራሪነት መካከል የሚደረግ ውድድር ይመስላል።አንዱ ከሌላው ጋር ለመሥራት ፍላጎት ያለው አይመስልም።ይህንን ማስቆም የሚችለው ደግሞ ማህበረሰቡ ነው።ካለፈው ተመክሮ በመነሳት ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ ብሎ ፊት ሊነሳቸው ይገባል።

ከሁሉም በላይ በአገርቤት የሚካሄደው የፋኖ ትግል የአማራ ሕዝባዊ ግንባርና ሕዝባዊ ልዩ ሃይል በሚል መጠሪያ መቅረቡ ልዩነት ያለ ያስመስለዋል።ለአጠራሩ የአደረጃጀትና የዓላማ ልዩነት ካለ ደግሞ ለእርስ በርስ ግጭት በር ይከፍታል።ስለሆነም የፋኖ ትግል በአንድ ሕዝባዊ ጦር(ሃይል)ስያሜና በጋራ አመራር ስር ቢሆን ለድሉ ዋስትና ይሆናል።ከመከፋፈልም ያድናል።ክፍተቶች ካሉ በጊዜው መደፈን አለባቸው። አሁን በመቀጣጠል ላይ ያለው ሕዝባዊ ትግል ላይ ውሃ እንዳይቸለስበት ካለፉት ልዩነቶች መማር ይገባል።ይህ ትግል ከተኮላሸ ደግሞ ለመጭው ብዙ ዓመታት የአነግና የወያኔ መጫወቻ መሆን ነው።የጠላቶቻችን መብዛት እንድንተባበርና በአንድነት እንድንቆም ያደርጉናል እንጂ በውሃ ቀጠነ

ወይም በግልና በቡድን ሽኩቻ እንድንተራመስ አያደርገንም።በብልጽግና ላይ ያለን አቋም አንድ መሆን አለበት።ያም መወገድ ያለበት ጠላት መሆኑን ማመንና መቀበል ነው።ስለሆነም ባኤዴንን እንደ ወገን ማዬትና ለመደራደር መሽኮርመም ትልቅ ስህተት ከመሆኑም በላይ በአገርና በሕዝብ ላይ የሚፈጸም ክህደት ነው።

ሌላው ጸረ አገርና ጸረ ሕዝብ የሆነው የጎሳ ፖለቲካ ከኢትዮጵያም ሆነ ከአፍሪካ መሬት ብቻም ሳይሆን ከምድር ገጽ ተነቅሎ መጥፋት አለበት የሚለው አቋም የሁሉም ሊሆን ይገባል።

ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ለኦሮሙማው ተረኛ አገዛዝ ለብልጽግና የሞራልና የሃሳብ ድጋፍ ሲቸሩ የነበሩት የግንቦት ሰባት ጀሌዎች አሁን የሕዝቡ ትግል እያደገ ሲመጣ የነበሩበትን ጎራ እዬለቀቁ ለዳግመኛ ጥፋት ውርውር በማለት ላይ ናቸው።በነዓምን ዘለቀና በአንዳርጋቸው ጽጌ የሚመራው ይህ ስብስብ ዓይኑን በጨው አጥቦ ከአማራው ፋኖ በላይ መስሎ ለመታዬት በመዳከር ላይ ነው።ባለበት ተቸንክሮ የቀረው የግንቦት ሰባቱ መሪ ብርሃኑ ነጋና የእሱ አፈቀላጤ የሆኑት ጋዜጠኞች ብቻ ናቸው።

መቼም የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ነው !ሰሞኑን የብልጽግና አገር አጥፊ ቡድን በሚኒስትሮች ካቢኔው የአማራ ክልል በኦነግ ጦር ሃይል እንዲወረር ያስተላለፈውን ውሳኔ እሱና የአብኑ  አድር ባይ በለጠ ሞላ ደግፈውታል።ብርሃኑ ነጋ የትምህርት ሚኒስትርነቱን ቦታ ከያዘ ጀምሮ ለሥርዓቱ የሚያደርገው ታማኝነት አይጣል ነው።የአማራውን ትግል የጥቂት ወሮበሎች እረብሻ ነው ከማለት ባለፈም  በሰሞኑ በጎንደር ተማሪዎች፣መምህራንና የትምህርት ቤት ዘበኞቼ ተገለውብኛል ሲል ጣቱን በፋኖ ላይ ቀስሯል። ፋኖ እንደ ኦነግ አሸባሪ ባንክ ቤት ሰብሮ ካዝና አይገለብጥም፤ንጹሃንን አይገልም፤መንገድ ዘግቶ አይዘርፍም፣ሕጻናትና አሮጊት ሴቶችን አይደፍርም፣የእምነት ተቋማትን አያቃጥልም፣፣ሕዝብ ንብረትና አገራዊ ተቋማትን አያወድምም።ሌላው ቀርቶ ለማረካቸው ሊገሉት ለመጡት የኦነግ ወራሪዎች በሰብአዊ አያያዝ የራሱን ስንቅ አካፍሎ የሚያበላ፣ የቆሰሉትን የሚያክምና የሚንከባከብ፣ እርህሩህና ፣የጦር ሜዳን ሕግ የሚያከብር የሕዝብ ሃይል ነው። ይህንንም ነጻ ባወጣቸው አካባቢዎች በስነምግባር የታነጸ መሆኑን  በግልጽ አሳይቷል። ይህንን የሕዝብ ልጅ ፋኖን ነው ወራዳው ብርሃኑ ነጋ በግድያ የወነጀለው።ይህ ወራዳ የትምህርት ሚኒስቴር 17 የአማራ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአብይ አህመድ የኦነግ ጦር ታፍነው ሲጠፉ የት ገቡ? ብሎ አልጠዬቀም።በጎንደር ከተማ  በኦነግ ወራሪ ሃይል 25 ተማሪዎች ሲጨፈጨፉ ድምጹን አላሰማም።አሁን ግን አማራው እንዲጨፈጨፍ በካቢኔ ስብሰባ ላይ እጁን ማውጣቱ ሰውዬው ካለው ሥር የሰደደ የአማራ ጥላቻ የመነጨ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ መጥቀስ አያስፈልግም።የሱ ነገር የበቃው ገና ከጧቱ አብይ አህመድን፣ለማ መገርሳንና ታከለ ኡማን አሻጋሪዎቻችን ናቸው ብሎ ለኦሮሙማው ቡድን የሰገደ እለት ነው።የጎባጣ አሽከር ጌታውን ለመምሰልልና ላለማጋለጥ አጎንብሶ ይሄዳል ይባላል፤ብርሃኑ ነጋና መሰሎቹ ከመጉበጥም አልፈው ጭራሽ ተንበርክከው ይሄዱ ይሆናል እንጂ ቀና ብለው አይሄዱም።

በመጨረሻ ለግንቦት ሰባት ተራ መንጋ የምናስተላልፈው ጥሪና መልእክት ቢኖር ለወሮበሎቹ ዳግም መጠቀሚያ ከመሆን ተጠንቀቁ፤ባለፈው ጊዜ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ላደረሳችሁት ጥፋት እንደአንዳንዶቹ ጓዶቻችሁ ወደ ህሊናችሁ ተመልሳችሁ ንስሃ ግቡ፤ወደ ሕዝቡ ተመለሱ፤አሁንም ተቃዋሚ በመምሰል በሚዲያ ለማወናበድ የሚሞክሩትን አትስሟቸው፤እነሱንም ከድርጊታችሁ ተቆጠቡ ብላችሁ ፊት ንሷቸው የሚል ነው።

የተግባር ሰዎች ይበለን! ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!